# የወንድም ከሓዲ ፪!

ለባዕድ ያወጡ ምስጢራቸውን
ለገንዘብ የሸጡ እናታቸውን
ዓይን-በዓይን የከዱ ሃገራቸውን

ዶክቶር ነን እያሉ፣ ነን ፕሮፌሰር
እነ ለፍቶ መና፣ ነግዶ መክሰር
ሞያቸው ለባዕድ በግልጽ ማቃጠር

ለጥቅም የተገዙ ከሓድያን ሞልተዋል
እጃቸውን ለግብፅ፣ ለባዕድ ሰጥተዋል
ለኣሜሪካም ሸንጎ ይግባኝ ኣቅርበዋል!

ዶክቶር፣ ፕሮፌሰር ኣጉል ንትርኩ
ጌታው ኣሜሪካ፣ ፈረንጅም ኣምላኩ
እጅግ የሚያሳዝን መጥፎ ነው ታሪኩ

የከሓዲ ዋጋ ዓይን የሚያሳውር
ኣምላኩን የካደ ለወርቅና ብር
ይሁዳ ኣስቆሮቱ ራሱ ይመስክር

HR-2003 ባንቺ ኣርሮ! ባንቺ ኣርሮ!
እግዜር ይሰውረን ከመዓት ዘንድሮ
ከወንድም ከሓዲ፣ ከምሁር ደንቆሮ…

ገ/ኢ. ጐርፉ።